DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የSY23-24፣ 'School Without Walls' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የመግቢያ ሂደት የደረጃ መጠን (Admissions Process Rubric)

ለክፍል ደረጃዎች፡ 9-12

**ስለ 'School Without Walls' የመግቢያ (Admissions) መስፈርት**: በ'School Without Walls' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስኬትን ያገኘ ተማሪ፤ ኃላፊነት የሚሰማው፣ ልበ-ሙሉ፣ ነገሮችን በቀደምትነት መጀመርን፣ በየቀኑ ወደትምህርት ቤት መምጣት፣ ለቀለም ትምህርት ትኩረት የሚሰጥ፣ እና የትምህርት አሰጣጥ አገልግሎታቸውን እንዲያገኙ የሚጠይቅ ነው። በተጨማሪም፣ በ'School Without Walls' ውስጥ ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች፤ ራሳቸውን የቻሉ፣ ጠንካራ የጊዜ አያያዝና አጠቃቀም ችሎታዎች ያላቸው፣ እና የዓለም ዙሪያ ዜጎች የመሆን ፍላጎት ያላቸው ናቸው።

**ስለ 'School Without Walls' የመግቢያ (Admissions) ሂደት:** በ'School Without Walls' ውስጥ፣ ከዚህ በፊት ከነበረው የትምህርት ዓመት የመጨረሻ ክፍሎቻቸው ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ፤ ሁሉም አመልካቾች ቢያንስ የ3.0 GPA ማግኘት አለባቸው። ለ 9ኛ ክፍል፣ ከፍተኛ ብቃት የGPA በሆነው ከ4.0 ነጥብ-ደረጃ (3.0 በዝቅተኛ/minimum የሚያስፈልግ ሆኖ) የተገኙ በላቀ-ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች፤ በቃለ-መጠይቁ እንዲካፈሉ ይጋበዛሉ። ለቃለ-መጠይቁ የሚጋበዙ ተማሪዎች፣ በሂደቱ ለማለፍ፣ በቃለ-መጠይቁ መሳተፍ አለባቸው። ከ10ኛ-12ተኛ ክፍል ለሚደረገው ቃለ-መጠይቅ፤ በመጪው የትምህርት ዓመት ይኖራል በሚኖሩት-የቦታዎች ቁጥር ላይ መሠረት-ያደረገ እና፣ በተቀበልናቸው የማመልከቻ ቁጥር ብዛት ላይ መሠረት ባደረገ-ሁኔታ ይካሄዳል። ከቃለ-መጠይቁ የውጤት ደረጃ (score) በተጨማሪ፣ በGPA ውጤታቸው ላይ መሠረት ያደረገን የውጤት ደረጃ (score)ን፤ ተማሪዎች ያገኛሉ።

እያንዳንዱ የመግቢያ (admissions) ሂደት ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሰረት የደረጃ ውጤት (scored) የሚሰጠው እና የሚለካ ይሆናል። የእነዚህ ሁለት የውጤት ደረጃዎች (scores) በአንድነት ተቀናጅተው፣ ለእያንዳንዱ ተማሪ የተጠራቀመ የማመልከቻ የውጤት ደረጃ (score)ን ያስገኛቸዋል። ቃለ-መጠይቁን ያጠናቀቁ ሁሉም ተማሪዎች፣ ብቁ የሚሆኑ እና በተጠራቀመው የማመልከቻ የውጤት ደረጃቸው (score) መሠረት፣ ደረጃ ይሰጣቸዋል።

| **የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች** | **መለኪያ (Weight)** | **ማስታወሻዎች፡** |
|---|---|---|
| የሪፖርት ካርድ ምልከታ<br><br>(ቢያንስ/Minimum የ3.0 GPA) | ማለፍ የሚገባው መስፈርት (Threshold criteria) | 'School Without Walls'፣ የክፍል ደረጃዎችን ብቻ እንደ ሪፖርት ካርድ ምልከታዎች አድርጎ ይመለከታቸዋል። በ'School Without Walls' ውስጥ የሚገቡ አመልካቾች፣ ጥብቅ እና ከባድ በሆነው ፕሮግራማችን ውስጥ መጪዎቹ ተማሪዎች፣ ስኬታማ ለመሆን ዝግጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፤ በቀድሞው የትምህርት ዓመት የመጨረሻው ሪፖርት ካርድ ላይ፣ የ3.0 GPA ወይም ከዚያ በላይ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። |

| | | |
|---|---|---|
| | | በ9ኛ ክፍል ውስጥ፣ የላቀ-ቦታ ላይ ያሉ ተማሪዎች - ከፍተኛ GPAs ደረጃ ያላቸው፣ ወደ ቃለ-መጠይቁ ይጋበዛሉ።<br><br>ባለፈው ዓመት GPAው እንዴት ተሰልቶ-እንደነበረ- ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት እዚህ ተመልከቱ፤ ይህም ለዚህም ለSY23-24 አንድ-ዓይነት በሆነ ሁኔታ የሚቀጥል-ይሆናል። |
| በ'GPA'ው መሠረት፣ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ፣ 3.0 ነጥብ ወይም ከዚያ በላይ ያመጡ፤ ከፍተኛ ደረጃን ያመጡ ተማሪዎች፣ በቃለ-መጠይቁ እንዲካፈሉ ይጋበዛሉ። | | |
| ቃለ-መጠይቅ | ~86% (31/ 36 ነጥቦች) | 'School Without Walls'፣ ለፕሮግራማችን የጋለ ስሜት ያላቸውን እና ለማህበረሰቡ ትጋትን የሚያሳዩ እንዲሁም ጽናትን የሚያሳዩ ተማሪዎችን ለይቶ ማውጣትን፣ አበክሮ ያምንበታል።<br><br>በGPA ውጤታቸውን መሠረት በማድረግ፣ ጎበዝ ተማሪዎች (Top students)፣ ከወላጅ/አሳዳጊያቸው ጋር፤ ወደ ፓናል ቃለ-መጠይቅ (panel interview) ይጋበዛሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ፣ ወላጅ/አሳዳጊ የውጤት-ደረጃ (score) አይደረግም። ፓናሉ (panel)፣ ፋክልቲን (faculty)፣ ሠራተኞችን፣ እና በአሁኑ ጊዜ የሚማሩ ተማሪዎችን ያካተተ ነው። ተማሪዎች እና ወላጆች ራሳቸውን በመሆን፣ የሚችሉትን ሁሉ እንዲያደርጉ እንጠይቃለን!<br><br>የሁሉም አመልካች ቃለ-መጠይቆች፣ በአንድ ዓይነት የውስጥ አሰራር የደረጃ መለኪያ (internal rubric)፣ ለ~86% የተማሪው የውጤት ደረጃ (score) በሆነ የቃለ-መጠይቅ ውጤቶችን መበቁጠር ይገመገማል።<br><br>በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት ባደረገ-መልኩ፤ ለSY23-24 ቃለ-መጠይቆች - እንደየአስፈላጊነቱ እና በሁኔታዎች-አመላካችነት ላይ መሠረት በማድረግ፣ በርቀት (virtually) የሚሆንበት ሁኔታ ሊኖር ይችል-ይሆናል። የጤና መመሪያን በመከተል እና በመቆጣጠር ላይ፣ ቁርጠኛ ሆኖ መስራቱን - DCPS ይቀጥልበታል። |
| የGPA የውጤት ደረጃ (Score) | ~14% (5/36 ነጥቦች) | ቃለ-መጠይቁን ያጠናቀቁ ሁሉም ተማሪዎች፣ በGPA ላይ መሠረት ያደረገ፣ ተጨማሪ የውጤት ደረጃ (score)፣ በሚከተለው መመዘኛ መሰረት ያገኛሉ፡<br>• 3.8 እና በላይ – 5 ነጥቦች<br>• 3.5 - 3.79– 4 ነጥቦች<br>• 3.2 - 3.49 – 3 ነጥቦች<br>• 3.0 - 3.19 – 2 ነጥቦች |

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

የቃለ-መጠይቅ እና የGPA የውጤት ደረጃዎች (scores)፣ በአንድ ላይ ተደምረው፣ እያንዳንዱን ተማሪ የተጠራቀመ የማመልከቻ የውጤት ደረጃ (score) ያስገኙዋል። ቃለ-መጠይቁን ያጠናቀቁ ሁሉም ተማሪዎች፣ ብቁ የሚሆኑ እና በተጠራቀመው የማመልከቻ የውጤት ደረጃ (score) መሠረት፣ ደረጃ ይሰጣቸዋል።